የምጽአቱ የምስራች

ቅጽ 84 ቁጥር 5(983)

“እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና” (ዮሐንስ 1፡16)

“ለሁላችንም ብርታት በሚሰጠው በክርስቶስ እንኑር” (በአንድሪው ሙሬ/Andrew Murray)

“ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ” (ማቴዎስ 28፡18)።

“በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ኀይሎት የበረታችሁ ሁኑ” (ኤፌሶን 6፡10)።

“ኃይሌ በድካምህ ይፈጸማልና” (2ኛ ቆሮንቶስ 12፡9)።

በእውነተኛ ክርስቲያኖች ዘንድ ድካማቸውን ከመቀበል የበለጠ ትልቅ ጉዳይ የለም። የእግዚአብሔር ሐሳብ ከሰዎች ሐሳብ እጅግ ከፍ ያለና የተለየ መሆኑ እውነትነት ያለበት ነው።

ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ ድካማቸውን ይዘነጋሉ። እግዚአብሔር ግን ይህን ድካማችንን ዘወትር በማስታወስ፣ በእርሱ ላይ እንድንታመን ይፈልጋል። ክርስቲያኖች ድካምና ፈተናን ድል በማድረግ መኖርን ይፈልጋሉ። እግዚአብሔርም በትክክል ይህ ድል እንዲኖረን ፈቃዱ ነው። ይህ ድልና እረፍት የሚገኘው በፈተናና በመከራ ውስጥ በማለፍ መሆኑን እግዚአብሔር በእንድ ልጁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል መከራ፣ ሞትና በትንሣኤው መሆኑን ያስተምረናል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመስቀል መከራ፣ ሞቱና ትንሣኤው በድል መነሣቱና ማረጉ ለእኛም መከራን በእርሱ ማለፍና በትንሣኤና በእርገቱ እንደምንከተለው አረጋግጦልናልና ይህ ሂደት ሊኖረን ይገባል (ሉቃስ 24፡49፤ ሐዋርያት 1፡8)።

ደቀ መዛሙርቱ ኃይልን ተቀበሉ

ደቀ መዛሙርቱ በጽኑ መከራ፣ መሰደድና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆነው በጽኑ ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ሲወድቁ፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ተቀብለዋል (ሐዋርያት 2፡4)።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በደቀ መዛሙርቱ ላይ በፈሰሰበት ወቅት፣ ከሰው አእምሮ በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሥራ በመካከላቸው ተከናወነ። በዚያ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ደቀ መዛሙርቱ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች የእግዚአብሔር ጉብኝትና በረከት አስተላላፊዎች ሆኑ።

የእግዚአብሔር አሠራር ከቃል እንደበት ያለፈ፣ በተግባር የሚታይ፣ የሰዎችን ክፉ ልብ የሚለወጥ፣ ማኅበረሰቡን ለበጎ ሥራ ሁሉ የሚያነሣሣና የሚያሰችል መሆኑን በተጨባጭ ያስመሰከረው በደቀ መዛሙርቱ ላይ የተጀመረውና እስከ ዛሬ ድረስ የቀጠለው ያመኑቱ ከእግዚአብሔር የሚቀበሉት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ነው (ሐዋርያት 2፡43፣ 4፡13፣ 5፡13)።

ዛሬም ይህን መልእክት የምናነብ ሁሉ ጌታን በብርቱ ጸሎትና በቅን ልብ ብንጠይቀው፣ ሙላቱን እናገኛለን።

መልእክት ከአሳታሚው ሪክ ካርማይክል (Rich Carmichael)

ክርስቶስ የጽናት ምንጭና መልካም ምሳሌ ነው

የዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከጌታ ያገኘሁት ትልቅ ቁምነገር በመከራና በችግር ውስጥ በጌታ ጽናት እንደሚገኝ ነው። “በትዕግሥት የዳኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፥ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና” (ያዕቆብ 5፡11)።

ይህን ክፍል ብዙ ጊዜ በማጥናት ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማጥናት የሚያበረታታና የሚያጽናና የእግዚአብሔርን በረከት አግኝቻለሁ።

የኢዮብ መከራ

ጻድቁ ኢዮብ ብዙ መከራ ያገኘው፣ ንብረቱንና ቤተሰቡን የራሱንም ጤና ያጣ ሰው ነበር። በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ግን በእግዚአብሔር ጸንቶ ነበር። ሚስቱ ይህ ሁሉ መከራ ሲደርስበት እግዚአብሔርን እንዲረግም ሰትወተውተው፣ አልቀበልም ብሉ በእምነቱ የጸና ጻድቅ ሰው ነበር። “ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን፥ ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን?” (ኢዮብ 2፡10)

የእግዚአብሔር ዓላማ ምሕረት ነው

በያዕቆብ መጽሐፍ እንደተገለጸው፣ በሕይወታችን እርሱ አውቆት የሚደርስ መከራ ሁሉ ዓላማና ምክንያት አለው። እግዚአብሔር የሚሆነው ሁሉ እንዲሆን የሚፈቅድና በመጨረሻው ለልጆቹ የተሻለውን ነገር የሚያደርግ መልካም አባትና ጌታ ነው (ኢዮብ 42፡5፣ 42፡10)።

የእግዚአብሔር አሠራር ለሰዎች አእምሮ የማይገባ ቢሆንም፣ በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ምሪት በቃሉ መገለጽ የእግዚአብሔር ዓላማ በጎና የሚያድን፣ ዘላለማዊ መሆኑን በሂደት እንረዳለን። ስለዚህም በእግዚአብሔር ሰዎች በነቢያቱ፣ በሐዋርያቱ፣ በደቀ መዛሙርቱና በጥንት ዘመን ክርስቲያኖች ላይ የደረሰውን ዛሬ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በአማኝ ልጆቹ ላይ የሚደርሱ ፈተናዎች፣ መከራዎችና ስደቶች ሁሉ እግዚአብሔር የሚያውቃቸው በውጤታቸውም የዘላለም ሕይወት የሚገኙባቸው መልካም መለኮታዊ አሠራሮች ናቸው።

“ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና። ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነትህ ብዙ ነው። ነፍሴ፦ እግዚአብሔር ዕድል ፈንታዬ ነው፤ ስለዚህ ተስፋ አደርገዋለሁ አለች” (ሰቆቃወ ኤርምያስ 3፡22)።

ስለዚህ በሚገጥመን መከራና ሥቃይ ችግር ሳንበገር፣ ጌታ የሰጠንን የወንጌል አደራ ለመፈጸም እንትጋ።

በእግዚአብሔር የተባረከ ሕይወት ምስጢሮች (በኤፍ. ቢ. ማየር/F.B. Meyer)

ለምትፈልጉት ጉዳይ የቃተታችሁበት ጊዜ አለን? ከሰይጣን ጋር ፊት ለፊት የተጋፈጣችሁ እስኪመስላችሁ ድረስ ሰይጣንን መገሠጽና ማሰወጣት ሲያቅታችሁ ወይም በዓለማውያን መካከል በሥራ ቦታ አፋችሁን በድፍረት ከፍታችሁ ለክርስቶስ መመስከር ያቃታችሁ ጊዜ አለን?

አዎን፣ በሁላችንም ሕይወት በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ እየተከሰተ፣ ኃጢአተኞችን ከክፉ መንገዳቸው መመለስ እያቃተን፣ የእኛም ሕይወት እየተዘበራረቀ፣ ሰዎች በዓይናችን ፊት ከጌታ ሳይተዋወቁ የሚያስናበቱበት ወቅት ይኖራል። ይህ ሁኔታ የሚከሰተው በእኛ ብቃትና ችሎታ ማነስ ሳይሆን፣ ይህንን የሚያስችለንን ጌታ ድካማችንን በመረዳት በጸሎት ባለመጠየቃችን፣ የየዕለቱ ጉዟችንን በቅዱስ ቃሉ በእምነት ባለማካሄዳችን የተነሣ ነው። “[በእግዚአብሔር] ለሚያምን ሁሉ ይቻላል” (ማርቆስ 9፡23)።

ትልቁ ጉዳይ እኛ የክርስቶስ ቅርንጫፎች መሆናችንን በመቀበል ከግንዱ ከክርስቶስ ጋር መጣበቅ ያለ መቻላችንና ቅርንጫፍ በራሱ እንዳች አቅም እንደሌለው ያለ መረዳታችን ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌያችን ሆኖ ከእግዚአብሔር ሙላት ተቀብልን መመላለስ እንዳለብን በፍጹም መዘንጋት አይኖርብንም (ቆላስይስ 1፡19)። የሰይጣንን፣ የዓለምንና የሥጋችንን ፈተናዎች ሁሉ በመቋቋም ለጌታ እንደሚገባው መሰጠትና ፍሬ ማፍራት የሚቻለን፣ ጌታችን እንዳስተማረን በሰማይና በምድር ከእግዚአብሔር ኃይልና ችሎታ እንደ ተሰጠን በመረዳት ነው (ማቴዎስ 28፡1)።

በዚህ ትልቅ መዋሃድ ከጌታ ጋር በቃሉና በመንፈስ ስንጣበቅ፣ እንዳች የሚሣነን ሳይኖር፣ የእምነት ድንቅ ሥራዎችና በረከቶች በሕይወታችን ይከሰታሉ።

በቅዱስ ቃሉ በመንፈስ ዘወትር እንድንሞላ የምንጠየቀው ሥጋችን ደካማ በመሆኑ፣ ሰይጣንም እኛን ለማጥቃት ስለሚጥርና ዓለም ከማታለል ስለማትመለስ ነው። ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት በጌታ እንመላለስ (ኤፌሶን 5፡18)።

የተለወጠ ሕይወት (በቻይና ሚሰዮናዊ ሀድሰን ቴይለር/By J. Hudson Taylor)

ለወራት በብዙ በረከቶችና ስኬቶች እቆይና ተመልሼ ምስጋና ቢስ በመሆን አጉረመርማለሁ፣ የጌታንም ብድራት እረሳለሁ። ሆኖም ግን፣ ለግሌ የሚያስፈልጉኝን ምግብና የመሳሰሉትን መፈለግና መጠየቅ ልጅምር ስሞክር፣ የተለመደው ምስጋና ከአፌ ሲወጣ፣ እንደ ገና ስኬትና ደስታ ውስጤን ይሞላል።

በየደቂቃው፣ በየቀኑና በየሰዓቱ ሊጥለኝ ሊያዋርደኝ የሚተጋውን ሰይጣንንና ሥጋዬን መርታት የምችለው ይህችን ቀንና እስትንፋሴን እስከ ዛሬ ያቆይልኝን ጌታዬን ለማመስገን አፌን ስከፍት በማገኘው የመንፈስ ቅዱስ ጉብኝት ነው።

እንዲህ ዘና ብዬ በሁሉም ነገሮቼ ላይ ሥልጣንና ኃላፊነት የሰጠኝ ማን ይሆን ብዬ ራሴን ሰጠይቅ፣ በቅዱስ ጥምቀት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኔና በእምነት የተቀበልኩት ጌታ የሰጠኝ ተስፋን በማመን እታደሳለሁ፣ እነቃቃለሁ። “ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው” (ዮሐንስ 1፡12)።

በየዕለቱ ኑሯችንና አገልግሎታችን ድካምና ቁዘማ ሊከሰት የሚችለው የምስጋናና የጸሎት ሕይወት ስናጣ፣ ከቃሉና ከኅብረት ስንርቅ ስለ ሆነ፣ በምንም ሁኔታ ውስጥ ብናልፍም እንኳ ጌታን ከማመስገን፣ ቃሉን ከማንበብና ከመጸለይ ችላ ማለት ፈጽሞ የለብንም።

ሁሉ በሁሉ የሆነውን የጌታን በረከት፣ ኃይልና ሰላም የምናገኘው ከጌታ ጋር ቆይታና መጣበቅ ሲኖረን በመሆኑ፣ ከጌታ የሚለዩንን የምንወዳቸውን ሰዎች ወይም አገልግሎቶችን ሳይቀር ጊዜ ስጥተን በማቆየት፣ መጀመሪያ ሰዎችንም ሆነ ሥራንና አገልግሎታችንን ሕይወትና ብቃት ሊሰጥ የሚችለውን ጌታን በቃሉና በጸሎት በምስጋና እንገናኝ።

“ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራለን፤ ብንጸና፥ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን” (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡13)። “እልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና” (ዕብራውያን 13:5)። የእግዚአብሔር በረከት የሚገኘው እርሱን ጌታን በክርስቶስ በመገናኘት ነው (ኤፌሶን 1፡8)።

በክርስቶስ መኖርና የቅድስና ምስጢር በትጋት ስለ መጸለይ

(በቶሬ/በሃሬት ስቶውና ሚልሺን ስናይደር/Harriet Stowe & Melvin Snyder)

ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ያለው ብቸኛ አማራጭ ጸሎት፣ ትዕግሥት፣ ጭምትነትና ማስተዋል ያለበት ሕይወት ነው። እነዚህን መሪ ቃላት ከወንጌሉ የምናገኝ ሲሆን፣ ቅርንጫፎች ከግንዱ ጋር ሲጣበቁ ሕይወትና እድገት እንደሚገጥማቸው ተረድተን፣ ከግንዱ

ከክርስቶስ ጋር በየዕለቱ በቃሉና በጸሎት መጣበቅ አለብን።

“በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዲይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም” (ዮሐንሰ 15፡4)።

ክርስቲያን እንዴት ፍሬ ሊያፈራ ይችላል? በትግልና በጥረት ነውን? በራሱ በሚያደርጋቸው ልምምዶች ነውን? አይደለም። ክርስቲያን ፍሬ እንዲያፈራ ቅርንጫፍ መሆኑን በማመን በግንዱ በክርስቶስ ላይ መጣበቅ እንደሚኖርበት ማወቅና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በቃሉና በጸሎት ከክርስቶስ ጋር መጣበቅ ይኖርበታል። ይህን በእምነት ተቀብሎ የሚደረጉ ጥረቶችና መንፈሳዊ ልምምዶች የሚፈለገውን ፍሬ በክርስቲያኑ ሕይወት ያስገኛሉ።

የቅድስና ምስጢር

የቅድስና ምስጢር ክርስቶስን በሚገባ ለተረዱትና ከክርስቶስ ጋር እንደሚገባ ለተጣበቁት የማይታወቅ ምስጢር መሆኑ ይቀርና ግልጽ በየቀኑ ለሁሉም የሚታይ የሕይወት ልምምድና ፍሬዎችን የሚያስከትል ይሆናል።

ንጉሥ ዳዊት በእግዚአብሔር እንደ ተወደደው፣ እኛ አማኞችም በእግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የተወደድን የሆንነው በእምነት ነው (ዮሐንሰ 3፡16)።

ንጉሥ ዳዊት በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት መኖር እንደ ተመኘው የእኛም ምኞት ይህ ከሆነልን፣ የቅድስናው ምስጢር የገባን የእግዚአብሔር ውዶች እንሆናለን (መዝሙረ ዳዊት 27፡4)።

ለሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ረብ የነበረውን ነገር ሁሉ እንደ ከንቱ ነገር በመቁጠር በክርስቶስ በማመን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሰንጠብቅ፣ የእግዚአብሔር ቅድስና ተካፋዮችና አካፋዮች እንሆናለን (ፊልጵስዮስ 3፡8)።

ክርስቶስ በእናንተ (በቻርለስ ስፐርጀን/Charles Spurgeon)

“ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምስጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገለጠእል [በክርስቶስ]” (ቆላሰይስ 1:26)።

ወንጌሉ ታላቁ ምስጢርና የምስጢሮች ሁሉ ምስጢር ነው። ይህ ወንጌል ትልቅ ምስጢር የተባለው ብዙዎች ለዘመናት ሲፈልጉት ያላገኙት የሁሉ ፈጣሪ ጌታ ክርስቶስ ማዕከሉ ስለ ሆነ ነው። ክርስቶስ ማዕከሉ ያልሆነበት፣ ክርስቶስ ራስና ዋና ያልሆነበትና የሌሎች የመላእክትና የቅዱሳን የታሪክ ትምህርት ክርስቶስን የሚሸፍነው ከሆነ፣ ይህ ትክክለኛ የክርስትና እምነትና ትምህርት አይደለም፣ አያድንም አያፈራም፤ ዘመን ጠብቆ ይጠፋል።

ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ፣ ስውም አምላክም፣ አማላጅም ተማላጅም የሆነ የሁሉ ፈጣሪና ጌታ ነው (ዮሐንስ 1፡14፤ ሮሜ 8፡34፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡5)።

ከሰው ሲወለድ መላእክት ለዘመሩለት ክብር በምድርና በሰማይ ይሁን! ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሳይወለድ በፊት እምቅድመ ዓለምም የነበረ አምላክ ነው (ዮሐንስ 1፡1)። “ሕጻን ተሰጥቶናል” ተብሎ ጌታችን ከቅድስት ማርያም ከመወለዱ 700 ዓመታት በፊት በትንቢት የተነገረለት የዘላለም አምላክና ድንቅ መካር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው (ኢሳይያስ 9፡6)።

በኃጢአት ምክንያት በሰይጣን ሤራ ከእግዚአብሔር የተለዩትንና የጠፉትን ሰዎች እግዚአብሔር ሊመልስ የላከው ከሴት የተወለደው ብቸኛው አዳኝ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዘፍጥረት 3፤ ገላትያ 4፡4)። በክርስቶስ ኢየሱስ እውቀት ቃል መንፈስ በተሞላን ቁጥር፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እየመሰልን ወደ እግዚአብሔር ዙፋን እንቀርባለን (ፊልጵስዮስ 3፡10፤ መክብብ 1፡7)።

ክርስቶስ አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ የሆነው ጌታ ለእኛ በቅዱስ ቃሉ ስለ ተሰጠን፣ እርሱን በእምነት ተቀብለን ለዘላለም መኖር መቻሉ ለእኛ በእርሱ ለምናምን ትልቅ ዕድልና በረከት ነው።

ክርስቶስ በእኛ ይኖራልን? እያልን በየቀኑ ራሳችንንና ሌሎችን እንጠይቅ። እዎን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ያው ነው (ዕብራውያን 13፡8)።

ኃጢአት መሥራታችሁን ጌታ መንፈስ ቅዱስ ባሳሰባችሁ ጊዜ ወዲያውኑ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመለሱና ተናዘዙ።

በኃጢአት ላይ ድል ስለ መቀዳጀትና በክርስቶስ አዲስ ሕይወት

(በኤፍ. ቢ. ማየርና ቻርለስ ስፐርጀን/F. B. Meyer and Charles Spurgeon)

እግዚአብሔር እኛ አማኞችን ከክርስቶስ ጋር በመሰቀል እንደ ተሠዋን ይመለከተናል። በክርስቶስ ኢየሱስ ከዓለም ኃጢአት በመውጣት ከሞት በትንሣኤው ወደ ክርስቶስ ክብር ገብተናል። እኛ ይህንን ባንረዳውም፣ በቅዱስ ቃሉ ላይ ከሞት ወደ ሕይወት በክርስቶስ መሻገራችን ተጽፎልናል።

ክርስቶስ ዛሬም እኔ ለኃጢአታችሁ ሞቼ በትንሣኤ ከኃጢአት አውጥቻችኋለሁ ይለናል። “እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ” (ወደ ሮሜ ሰዎች 6፡11)።

ኃጢአት መሥራታችሁን ጌታ መንፈስ ቅዱስ ባሳሰባችሁ ጊዜ ወዲያውኑ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ። ጫጩት ከክፉ አውሬ በእናቷ ክንፎች እንደምትሸሸግ፣ በክርስቶስ ውስጥ ተሸሸጉ። ኃጢአታችሁን በማቃለል፣ ሁሉም ያደርገዋል በማለት የንስሐ ጊዜን በማራዘም አትጥፉ።

ጌታችን በእርሱ ያመኑትን አይጥልም፣ አያሳፍርምና በኃጢአት፣ በድካምና በሰንፍና ስትገኙ፣ የመንፈስ ቅዱስን ወቀሳ ችላ ሳትሉ ወደ ጌታ ምሕረት በንስሐ ፈጥናችሁ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ። “ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ፥ በክብሩም ፊት በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ ለሚችለው ብቻውን ለሆነ . . . ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ይሁን” (የይሁዳ መልእክት 24)።

“ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?” (ሮሜ 6፡3)። ክርስቶስ አዲስ ሕይወትን ከሰጠን በኋላ እሮጌው እኛነታችን ሊገዛን ይገባልን? በእሮጌው አዳም ሳለን እንደ ፈለግን በኃጢአት መቀጠል ሰንችል፣ በአዲሱ አዳም በክርስቶስ ካመንን ግን ኃጢአትን ፈጽሞ መለማመድ የለብንም።

ሁል ጊዜ በኃጢአት ልምምድ ከተያዝን፣ መለወጣችን የት አለ? በምኞት በሥጋ ፈቃድ በኃጢአት እንዳንቀጥል ቅድሰናን ለሚያጎናጽፈን ለክርስቶስ ራሳችንን በሚገባ በማቅረብ ሥጋችንን በጾምና በጸሎት፣ ዓይኖቻችንንና እግሮቻችንን ከክፉ መንገድ በመጠበቅ እንኑር። ክርስትና በቃልና በጥቅስ ብቻ የሚኖርበት ሳይሆን፣ በጭምትነትና በእርጋታ ሥጋን በመጎሰም፣ እንደበትን በመግራት፣ ከዓለም በመለየት፣ የሰይጣንን ሥራዎች በቃሉና በጾም ጸሎት በመፋለም የሚኖሩት ሕይወት ነው።

ጸጋ ተሰጥቶናል፣ እንዴ መዳን ካገኘን ምንም አንጠፋም የሚል የክርስቶስ ትምህርት የለንም፤ እንጠንቀቅ።

ክርስቶስ መጀመሪያ ወደዳችሁ (በጆርጅ ዋይት ፊልድ/George Whitefield)

የክርስቶስ ፍቅር በሕይወታችሁ ሁሉ እንዲሞላ እርሱ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ልንወደድ የማይገባን ኃጢአተኞችን ወደናልና እንውደደው፣ እንከተለው። ክርስቶስ መጀመሪያ ሲጠራን የእኛን ብቃትና መልካም ሥራ አይቶ ሳይሆን፣

እንዲሁ በዘላለም ፍቅር ሊያድነን ስለ ፈለገ ጠራን፣ ለየን።

የክርስቶስ ፍቅር ከፍታውና ጥልቀቱ እጅግ ሊለካ የማይችል፣ ከልብ ለልብ የሆነ፣ አጥንትና ልብን ዘልቆ የሚደርስ ቅዱስ ንጹሕ ፍቅር ነው። ከዚህ ከክርስቶስ ፍቅር ችግር፣ መከራ፣ ደስታ ፣ ከፍታ፣ ዝቅታ፣ ሥልጣናት፣ ወጀብ፣ ዓውሎ ንፋስ፣ መንግሥታት፣ እታላዮች፣ የፍቅር-ነዋይ ሸቃጮች፣ ማንም ቢሆን ሊለየን አይችልም። በዚህ ልዩ ፍቅር ዘወትር እንመላለስ፤ ይህንን ፍቅርም ለሌሎች ለማያውቁት እንመስክር። “ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?” (ወደ ሮሜ 8፡38)

የምጽአቱ የምሥራች የቀድሞ አገልጋዮች እረፍት

“መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ” (ማቴዎስ 25፡21)። የምጽአቱ የምስራች የሮማንያ ትርጉም አስተባባሪ እኅታችን ካሮል ግሩትጀን ቪልዝና የግብፅ የዓረብኛው እትም አስተባባሪ ወንድማችን ሳሚር ሳዲቅ በቅርቡ ወደሚወዳቸውና ወደሚወዱት አባታቸውና ጌታቸው ክርስቶስ እቅፍ ገብተዋል፣ ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል።

ካሮል ከ1997 ጀምሮ በሮማንያ የወንጌል ሚሲዮናዊ በመሆን ማገልገል ስትጀምር፣ በ1998 የመጀመሪያውን የሮማንያ የምጽአቱ የምሥራች ትርጉም በማዘጋጀት እስከ ዕለተ ሞቷ በመልካም ሰታገለግል ቆይታለች። ወንድማችን ሳሚር እንደዚሁ ከባለቤቱ ጋር በ1997 ወደ ግብፅ ከተጓዙ በኋላ፣ በ2002 የዓረብኛውን የምጽአቱ የምሥራች ትርጉም ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ሲያገለግል ቆይቷል። ጌታ በእነዚህ ወገኖች የተዘራውን ወንጌል ፍሬ ይሰጥ፤ የሚተኳቸውንም ያሰነሣ ዘንድ እንጸልይ።

የወንጌል ሚሰዮናዊነት ዘላለማዊ ሥራ ነው

(በአስተባባሪው ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ)

“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሰም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፣ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ” (ማቴዎስ 28፡19)።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ታላቁን ትእዛዝ ታላቁ ተልዕኮ ብሎ ያስተማረን ሰዎችን ሁሉ እያጠመቅንና እያስተማርን የዘላለም ሕይወት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው።

በሀገራችን ኢትዮጵያም ይህንን የጌታ ትእዛዝ ከመጀመሪያው ጀምሮ የተቀበሉ እንደ ነበሩ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል (የሐዋርያት ሥራ 8፡26)።

ሆኖም ግን፣ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያው በትንቢት እንዳስጠነቀቀው፣ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች በንጉሥ በቄሳር ሥልጣን ጥማት የተቀላቀሉ መንጋውን (ምእመኑን) ለመብላት ከክርስቶስ የእውነት ትምህርት እየተሳሳተ እየተዳፈነ ክርስትና በዓለም ሁሉ ሳተ (የሐዋርያት ሥራ 20፡29)።

ሆኖም ግን፣ ጌታ ለሕዝቡ ስለሚያስብ፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ለመመለስ የተሐድሶ አስተማሪዎችን በዓለም ዙሪያ አስነሣ። በሀገራችን ኢትዮጵያ በትግራይ ቆየጻ አጋሜ ደቅ እስጢፋኖስ የተባለው መነኩሴና ተከታዮቹ ነበሩ።

ደቅ እስጢፋኖስ በክፉ ሥጋዊ ቀሳውስት ተከሰሶ በጊዜው መንግሥቱና ሀገሩ በሃይማኖት ስበብ እንዳይፈርስ በስጋው በንጉሥ ዘርዓያዕቆብ በአሠቃቂ ሁኔታ የሞት ፍርድ ተበየነባቸው። የጀመሩት ቅን ራእይ ቀጥሎ ለወንጌል ሥራ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በሀገር ተወላጅ ከነአለቃ ዘነብ፣ አለቃ ታዬ፣ አለቃ ተወልደመድኅን፣ ወንጌላዊ ሂካ ኦነሲሞስ ነሲብ የወንጌል ተሐድሶ ቀጥሎ ለዚህ ዘመን ደርሷል።

ይህንን የሚሰዮን ወንጌል ሥራ በትክክል ከራሳችን ሕዝብ የበለጠ ሰለሌለ፣ ወንጌሉ የገባን በእውነትና በመንፈስ እንቀጥለው፣ እንጸልይ እንትጋ እናገልግል።

የእንባቢዎች ምስክርነቶች

ከአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ለብዙ ዓመታት የሚላክልኝ የምጽአቱ የምሥራች በማተሚያ ቤት የተዘጋጀው ደርሶኛል። ጌታ አገልግሎታችሁን ሁሉ ይባርክላችሁ፣ በጸሎትና በሚቻለኝ እደግፋችኋለሁ።

ሐዋሳ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ

የምጽአቱ የምስራች ዘወትር የሚያነቃቃኝ የነፍሴ ምግብ ነው፤ ተባረኩልኝ!

ከመቱ፣ ኢሉ አባቦራ

የምጽአቱ የምሥራች በአበረታች መልእክቷ ድጋሚ ከከተማችን በመድረሷ ጌታን አመስግናለሁ፤ ሳታቋርጡ መላኩን ቀጥሉበት።

የመዳን ምክሮችና ምስክርነቶች

የሰው ዘር እግዚአብሔር በእምሳሉ ከፈጠረው በኋላ በሰይጣን አሳሳችነት ከእግዚአብሔር ሰለ ተለየ፣ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ከውድቀት በኋላ ከሴቲቱ የሚወለደውና በትንቢት “የሰይጣንን ራስ ይቀጠቅጣል” የተባለው የክርስቶስ ተከታዮች ከእግዚአብሔር ጋር የተጣላውን ሰው አስታራቂ ናቸው (ዘፍጥረት 3፡15)።

በዚህ የእግዚአብሔር የቀደመ የተሰፋ ቃል ኪዳን መሠረት ከሴት የተወለደውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አማኞች ሁሉ እንዲመስክሩና ሰዎችን ከጥፋት እንዲመልሱ አደራም ኃላፊነትም ተሰጥቷቸዋል።

ይህ የምስክርነት አገልግሎት መናገር የሚችሉ ብቻ ሳይሆን፣ የሁሉም አማኞች ኃላፊነትና ጥቅም ነውና ክርስቶስን ላላወቁት ሁሉ እንመስክር (ሐዋርያት 1፡8)።

የመዳን ምክሮች

1. ኃጢአተኛ ለመሆናችን ቅዱስ ቃሉን በሰማን ጊዜና ያመኑት ክርስቶስን ተቀበሉ ሲሉን፣ በጌታ ቃል መሠረት ንስሐ ገብተን ክርስቶስን እንመነው፣ እንቀበለው (ዮሐንስ 1፡12፤ ሮሜ 3፡23፣ 6፡23)።
2. የእግዚአብሔርን ይቅርታ በንስሐ ከተቀበልን በኋላ፣ ከክፉ መንገዳችንና ኃጢአተኛ ተግባራችንና ልማዳችን እንመለስ (ኢሳይያስ 55፡7)።
3. ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታችንና አዳኛቸን መሆኑን ካመንን በኋላ፣ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በአንድ አምላክ ከሚያጠምቁና ከሚያምኑ ወገኖች ጋር ለኅብረት እንቀላቀል (ማቴዎስ 28፡19)።

ዓለም አቀፍ የጸሎት ርእሶችና የህገሮች መረጃ

የወንጌል ሥራ ከመጀመሪያው ጀምሮ በጸሎት ተካሂዷል

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ በሕይወቱ በምድር ሳለ ያስተማረን ዘወትር የጸሎት አርበኛና ጌታ መሆኑን ነው (ማርቆስ 1፡35፣ ሉቃስ 23፡34)።

እኛም የክርስቶስ ተከታዮች በጌታችን ፈለግ ሕይወታችን በሙሉ በጸሎት የተሞላ፣ እያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን ሁሉ በጸሎት ሊጀመር ሊካሄድና ሊጠናቀቅ፣ በመጨረሻም በምስጋና ሊቋጭ እንደሚገባ የጌታ ቃልና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስተምሩናል፣ የራሳችን ሕይወታችንም ያሳየናል።

በዚህ ወቅት ከፍተኛ የሕዝብ ብዘት ላላቸውና ኢየሱስ ክርስቶስን ሕዝባቸው ለማያውቅ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ህገራትና በሕዝቧ ብዛት ከአፍሪካ 2ኛ ለሆነችው፣ ችግርና መከራዋ ለበዛ

ለሀገራችን ኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ እንድንጸልይ የዝግጅት ክፍሉ ያሳስባል።

ሕንድ

በዓለም በሕዝብ ብዛት 1ኛ፤ 1 ቢሊዮን 458ሺህ። አብዛኛዎቹ ሕዝቦቿ የሂንዱ የመናፍስት አምልኮ ተከታይ የሆኑ ናቸው።

ቻይና

በሕዝብ ብዛት ከዓለም 2ኛ ስትሆን፣ 1 ቢሊዮን 398ሺህ። ወንጌል አማኞቹ 7.6 ከመቶ ሲሆኑ፣ አብዛኛው ሕዝቧ ሃይማኖት-የለሽ ናቸው።

ናይጄሪያ

የሕዝብ ብዛት ከአፍሪካ 1ኛ፤ 236 ሚሊዮን 759ሺህ፤ ወንጌል አማኞች 26 ከመቶ ናቸው።

ኢትዮጵያ

ከአፍሪካ በሕዝቧ ብዛት 2ኛ፤ 135 ሚሊዮን 251ሺህ ሲሆን፣ ወንጌል አማኞች 18 ከመቶ ናቸው።

ቱርክ

የመጀመሪያዎቹ የክርስቲያኖች ማዕከል ሕዝቧ 86 ሚሊዮን 820ሺህ ሲሆን፣ ምንም ወንጌል አማኞች የሌሉባት ሆናለች።

የሰሜን አፍሪካ ሀገሮች

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ማዕከል፣ ትክክለኞቹ ቅዱሳት መጻሕፍት የተሰባሰቡባት፣ የክርስትና በኩር አስተማሪዎች የነበሩባት፣ ወንጌል አማኞች ከ5 ከመቶ በታች ናቸው።

ለሁሉም ብርቱ ጸሎት ይካሄድ።

የምጽአቱ የምሥራች ማስታወቂያዎችና ማሳሳቢያዎች

ለአፍሪካ ቀንድ ምሥራቅ አፍሪካ ጸሎት

የእንግሊዘኛው እትም በደረሳቸው ዓለም አቀፍ መረጃ መሠረት ለአፍሪካ ቀንድ ምሥራቅ አፍሪካ ለተባባሰው ፍጥጫ ብርቱ ጸሎት አቅርበዋል፣ እንጸልይበት።

የሕዳሴው ግድብ

በሀገራችን ኢትዮጵያ የአባይ ወንዝ መፍለቂያና ከ80 ከመቶ በላይ ውኃውን ከለም አፈሯ ጋር ወደ ሌሎች ሀገሮች፣ በተለይ ግብፅ፣ የሚወስደው የአባይ ወንዛችን በጌታ ድጋፍ ተገድቦ ለሕዝባችን ጥቅም በመዋሉ ለጌታ እጅግ ሰፊ ምስጋና እናቅርብ።

የመገናኛ ብዙኃንን በጸሎት እናስብ

ለሕዝባችን ትክክለኛ ዜና ያቀርቡ ዘንድ የመገናኛ ብዙኃን ሠራተኞችን የእውነት መንፈስ እንዲመራቸው እንጸልይ። የሰዎችን ግፍ የቀድሞው ባርነትና ቅኝ ገዥነት በረቀቀ ዘዴ በክርስትና እምነት ሰም እያሰፋፋ ሰዎችን የሚያስቱ፣ እንዴ ዘር ከሌለው እንዲጣላ የሚቀሰቅሱትን ጌታ እንዲገታ እንጸልይ። እኛም በጎነትና እውነት ያለበትን ዜና እናቅርብ፣ ለተገፉትም እንጩኽ፣ እንጸልይ።

ለአማርኛው ትርጉም አንባቢዎች

የምጽአቱ የምሥራች የክርስቶስን ወንጌል ለሕዝባችን በሚገባው ቋንቋ እየተረጎመ የሚያቀርብ የበጎ ፈቃድ የወንጌል አገልግሎት ነው።

የአገልግሎቱ ብቸኛ ገቢ የአንባቢያን ሰጦታ በመሆኑ፣ የአቅማችሁን በፖስታ ቤት ሀዋላ በአድራሻችን በመላክ ይህን ክቡር የጌታ አገልግሎት ደግፉ፤ በጸሎታችሁም አስቡን።

ከአስተባባሪው

ለሁላችሁም በግል ለመመለስ ጊዜና አቅም ስለሌለን፣ በዚሁ ምስጋናችን ይድረሳችሁ። ለዚህ ክቡር አገልግሎት በጸሎትና በሚቻላችሁ ድጋፋችሁን እንጠይቃለን።

የምጽአቱ የምስራች የወንጌል አገልግሎት
አስተባባሪ፦ ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ - በኢትዮጵያ ተጠሪ፦ ብርሃኑ ጥርሰማ
ሰልክ፦ 0993154034

አርታዒ፦ ዘነበ ገብረሐና
ታይፕና ዲዛይን፦ አቤኔዘር ጽሕፈት ሥራ፤ መካኒሳ

የምጽአቱ የምስራች አገልግሎት
Amharic Herald of His Coming
የፖ.ሣ.ቁ /P.O.Box/ 8986
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

በሶላር ማተሚያ የታተመ

በነጻ የሚሰራጭ